# ደግሞም ለበርጩማ!

(ከዓሊ. ሁሴን፣ ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ. ም.)




እኛ ባወጣነው፣ ህግና መመሪያ፣
እስከተወራጨ፣ በዚያ ክብ ዙሪያ፣
ያውም ለመቀመጥ፣ ደሞም ለበርጩማ፣
ይምጡ ይዘፍዘፉ፣ ሰፊ ነው ፓርላማ!
እንኳን የእኛ ቁጣ፣ የተዋሃዳቸው፣
ፓርላማ ውስጥ ያሉት፣ ተቃዋሚ ያልናቸው፣
ሌሎቹም በመድረክ፣ ከዚያም ዝቅ ካሉ፣
ደስ ይለናል ይምጡ፣ ምርጫ ይካፈሉ!!
ከተጠናቀቀው፣ ካለቀው ድግሱ፣
'ር ጋፊ ለመልቀም፣ ከተግበሰበሱ፣
ያውም ለመቀመጥ፣ ደሞም ለበርጩማ፣
ይምጡ ይዘፍዘፉ፣ ሰፊ ነው ፓርላማ!

ባለ አንድ ኢንች ጮማ፣ መቁረጥ ጥሬ ስጋ፣
ምርጥ ውስኪ መለጋት፣ በጠባ በነጋ፣
ተቀምጦ ማዛጋት፣ ከወንበር መለጠፍ፣
ህልም እስከሚያዩ፣ ተኝቶ ማንኳረፍ፣
አንዳንዴ ሲነቁ፣ ድንገት ሲባንኑ፣
እኛ የተፋነውን፣ ቃል እየዘገኑ፣
መልሶ ከመርጨት፣ ሌላ ምን አላቸው?!
አይጎዱንም ይምጡ፣ የዋህ በጎች ናቸው!!

ሕዝብ ሰልፍ ማስወጣት፣ ስራ ማቆም አድማ፣
አመጽ ማነሳሳት፣ ከገጠር ከተማ፣
ስርዓቱን መቀየር፣ መንፈስ ከሌላቸው፣
ሰላማዊ ትግል፣ በደንብ የገባቸው፣
የምንገለው ሞቶ፣ ቀሪው እንባ ቢራጭ፣
ያፈነውም ጠፍቶ፣ ቀሪው ህልሙን አማጭ፣
ይበጠስ ሰንሰለት፣ ቢል ግፉን አስደማጭ፣
ለእርሳስ አያስቡ፣ አለያም ለምላጪ፣
ተቃውሞ አያሰሙ፣ በሕፃናት ሽያጪ፣
የሚስማማን አንቀጽ፣ ተነድፎ ቢቀመጥ፣
በደሞዛቸው ላይ፣ እስካልመጣ ለውጥ፣
እኛ በነሱ ላይ፣ እነሱ በወንበር፣
ከፓርላማ ገብተው፣ እስከመራን አገር፣
ከዚህ የበለጠ፣ ምን አለ የሚያስማማ፣
ይግቡ ይቀመጡ፣ ደግሞ ለበርጩማ!!

የነሱ መፈክር፣ ጠዋትና ማታ፣
ብር እስካስቆጠረች፣ እስካለች ልዴታ፣
እኛ ምን ደንታ አለን፣ ርሃብ ሰው ቢጨርስ፣
ሀገር ድንበር ቢፈርስ፣
የምቾት ጥላችን፣ ደሞዝ ከፋያችን፣
እስካለልን መለስ!!!
ይሄን ስለሆነ፣ የሚያውቁት መዝሙር፣
ይምጡ ለምርጫችን፣ ይግቡ ይሳተፉ፣
የለብንም ችግር!!
ይልቅስ ጠንክሮ፣ አበክሮ መስራት፣
በህቡዕ ያለውን፣ ዋነኛውን ጠላት፣
ደጋፊ ማሳጣት፣ ታሪኩን አጉድፎ፣
ባልጠበቅነው መንገድ፣ እንዳይደፋን ጠልፎ፣
ሕጋዊ እየሆነ፣ ምርጫ አልገባም ላለው፣
ከውስጡ አንጃ ፈጥሮ፣ ከፍሎ ማዳከም ነው፣
ይከበር ልደቱ፣ ይቀጣጠል ሻማ፣
ይምጡ ይሰግሰጉ፣ ገብተው ከፓርላማ፣
እኛ ምን ቸግሮን፣ ደግሞ ለበርጩማ!!!